# የኢትዮጵያ ኢነርጂ ባለስልጣን

# ለኤሌክትሪክና ኤሌክትሪክ ነክ ለሆኑ የንግድ ሥራ መስኮች የብቃት ማረጋገጫ ለመመሰን ተሻሽሎ የወጣ ጊዜያዊ መመሪያ ቁጥር 1/2010

ሐምሌ 2010 ዓ.ም

አዲስ አበባ

መጋቢት 2010 የንግድ ሚኒስቴር ብቃት ማረጋገጫ የሚሰጥባቸዉ የንድ ሥራ ዋና ዘርፎችን እና የብቃት ማረጋገጫ ሰጪ መ/ቤቶች ለይቶ የላከዉን መመሪያ መነሻ በማድረግ የነበረዉን ጊዜያዊ መመሪያን ለመተካት ተሻሽለዉ የወጣ መመሪያ ነዉ፡፡

# ክፍል አንድ
# ጠቅላላ

1. *አውጪው ባለሥልጣን*

የኢትዮጵያ ኢነርጂ ባለስልጣን በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 980/2008 በተሰጠው ሥልጣን መሰረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

*1. አጭር ርዕስ*

ይህ መመሪያ ኤሌክትሪክና ኤሌክትሪክ ነክ ለሆኑ የንግድ ሥራ መስኮች የንግድ ብቃት ማርጋገጫ መስፈርቶችን ለመወሰን ተሸሽሎ የወጣ መመሪያ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

*1.1 ዓላማ*

ይህ መመሪያ በአዋጅ ቁጥር 980/2008 መሰረት በኤሌክትሪክ እና ኤሌክትሪክ ነክ ለሆኑ የንግድ ሥራ መስኮች የንግድ ብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ለማግኘት መሟላት የሚገባቸዉን መስፈርቶች በማዘጋጀት ለህብረተሰቡ የሚቀርቡ ምርቶችና አገልግሎቶች ጥራትና ደረጃቸዉን የጠበቁ ሆነዉ የህብረተሰቡን ሀብት እና ደህንነት ለመጠበቅ እንዲያስችሉ ነዉ፡፡

*1.2 ትርጓሜ*

በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 980/2008 የተቀመጡት ትርጓሜዎች እንደተጠበቁ ሆነዉ ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም፣

1.3 "ኤሌክትሪክ " ማለት ከዉኃ ኃይል፣ ፀሐይ ኃይል፣ ከነፋስ ሀይል ከከርሰ ምድር እንፋሎት ወይም ከሌላ ምንጭ የሚገኝ የኤሌክትሪክ ጉልበት ወይም ሃይል ነዉ፡፡

1.4 "የኤሌክትሮሜካኒካል ሥራ" ማለት፡ የአሳንሰር፣ ተንሳቃሽ ደረጃዎች ፣የኢንዱስትሪ እና የቢሮ የአየር የሙቀትና ቅዝቃዜ ልኬት ማስተካከያ መገልገያዎች፣የኢንዱስትሪ መሳሪያዎች፣ የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ፣ማስተላለፊያ፣ ማከፋፈያ፣ ማሰራጫ ጣቢያዎች ፣ መስመሮች እና ሌሎች ተመሳሳይ ሥራ ዎች ተከላና ጥገና ነዉ፡፡

1.5 "ባለስልጣን (ኢ.ኢ.ባ)" ማለት በኢነርጂ አዋጅ ቁጥር 810/2006 መሰረት የተቋቋመዉ የኢትዮጵያ ኢነርጂ ባለስልጣን ነዉ።

## ክፍል ሁለት
## የሥራ ተቋራጭ ደረጃዎች

### 2. የኤሌክትሪክ ስራ ተቋራጭ (50320)

የኤሌክትሪክ ሥራ ተቋራጭነት ስምንት የሥራ ደረጃዎች ይኖሩታል።

2.1 የኤሌክትሪክ ስራ ተቋራጭደረጃ 1፣

2.2 የኤሌክትሪክ ስራ ተቋራጭደረጃ 2፣

2.3 የኤሌክትሪክ ስራ ተቋራጭደረጃ 3፣

2.4 የኤሌክትሪክ ስራ ተቋራጭደረጃ 4፣

2.5 የኤሌክትሪክ ስራ ተቋራጭደረጃ 5፣

2.6 የኤሌክትሪክ ስራ ተቋራጭደረጃ 6፣

2.7 የኤሌክትሪክ ስራ ተቋራጭደረጃ 7፣

2.8 የኤሌክትሪክ ስራ ተቋራጭደረጃ 8፡

እያንዳንዱ የኤሌክትሪክ ሥራ ተቋራጭ ደረጃ የሚከተሉት ሥራዎች ይኖሩታል።

### 2.1 የኤሌክትሪክ ስራ ተቋራጭደረጃ 1

ሀ. አጠቃላይ የማመንጨት አቅም ከ100 ሜጋዋት በላይ ኃይል ያላቸው ማንኛቸውንም የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ ተቋማት የኤሌክትሪክ ግንባታ ሥራ አገልግሎት በሙሉ፣

ለ. ከ86 ኬቪ. በላይ የሆኑ ማንኛቸውንም የኃይል ማስተላለፊያና የማከፋፈያ መስመሮች/ጣቢያዎች ግንባታ ሥራ አገልግሎት በሙሉ፣

ሐ. ከዚህ ደረጃ በታች ያሉ የሌሎች ኤሌክትሪክ ሥራዎችን በሙሉ ያካትታል።

2.1.1 ለኤሌክትሪክ ስራ ተቋራጭ ደረጃ አንድ ከዚህ በታች በዝርዝር የተቀመጠው የሰው ኃይል መስፈርት መሟላት ይኖርበታል፣

ሀ. የኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽን ስራዎች የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ከኢ.ኢ.ባ ደረጃ "ሀ" ያለው/ያላት ባለሙያ ብዛት አንድ፣



የኢትዮጵያ ፌደራል ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የኢትዮጵያ ኢነርጂ ባለስልጣን Federal Democratic Republic of Ethiopia Ethiopia Energy Authority

ለ. የኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽን ስራዎች የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ከኢ.ኢ.ባ ደረጃ "መ" ያለው/ያላት ባለሙያ ብዛት አንድ፣

ሐ. የኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽን ስራዎች የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ከኢ.ኢ.ባ ደረጃ "ሠ " ያለው/ያላት ባለሙያ ብዛት አንድ።

❖ ከዚህ በላይ በተቀመጠው የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ያላቸው ሁለት ባለሙያዎች ማለትም/ ደረጃ "ሀ" እና "ለ" ወይም ሁለት ደረጃ "ሀ"/ ያቀረበ ድርጅት ተጨማሪ አንድ ኤሌክትሪካል መሀንዲስ/ ኤሌክትሪሽያን /ማቅረብ ይኖርበታል።

## 2.2 የኤሌክትሪክ ስራ ተቋራጭደረጃ 2

ሀ. አጠቃላይ የማመንጨት አቅም እስከ 100 ሜጋ ዋት የኃይል አቅም ያላቸው ማንኛቸውንም የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ ተቋማት የኤሌክትሪክ ግንባታ ሥራ አገልግሎት በሙሉ፣

ለ. እስከ 86 ኬቪ. የሚደርሱ ማንኛቸውንም የኃይል ማስተላለፊያና ማከፋፈያ መስመሮች/ጣቢያዎች ግንባታ ሥራ አገልግሎት በሙሉ፣

ሐ. ከዚህ ደረጃ በታች ያሉ ሌሎች የኤሌክትሪክ ሥራዎችን በሙሉ ያካትታል።

2.2.1 ለኤሌክትሪክ ስራ ተቋራጭ ደረጃ 2 ከዚህ በታች በዝርዝር የተቀመጠው የሰው ኃይል መስፈርት መሟላት ይኖርበታል፣

ሀ. የኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽን ስራዎች የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ከኢ.ኢ.ባ ደረጃ "ሀ" ያለው/ያላት ባለሙያ ብዛት አንድ፣

ለ. የኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽን ስራዎች የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ከኢ.ኢ.ባ ደረጃ "መ" ያለው/ያላት ባለሙያ ብዛት አንድ፣

## 2.3 የኤሌክትሪክ ስራ ተቋራጭደረጃ 3

ሀ. አጠቃላይ የማመንጨት አቅም እስከ 10 ሜጋ ዋት ኃይል ያላቸው ማንኛቸውንም የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ ተቋማት የኤሌክትሪክ ግንባታ ሥራ አገልግሎት በሙሉ፣

ለ. እስከ 86 ኬቪ. የሚደርሱ ማንኛቸውንም የኃይል ማስተላለፊያ መስመሮችና ማከፋፈያዎች ግንባታ ሥራ አገልግሎት በሙሉ፣

ሐ. ከዚህ ደረጃ በታች ያሉ ሌሎች የኤሌክትሪክ ሥራዎችን በሙሉ ያካትታል።

2.3.1 ለኤሌክትሪክ ስራ ተቋራጭ ደረጃ 3 ከዚህ በታች በዝርዝር የተቀመጠው የሰው ኃይል መስፈርት መሟላት ይኖርበታል፣

ሀ. የኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽን ስራዎች የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ከኢ.ኢ.ባ ደረጃ "ሀ" ያለው/ያላት ባለሙያ፣ ብዛት አንድ፣

ለ. የኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽን ስራዎች የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀትከኢ.ኢ.ባ ደረጃ "ሠ"ያለው/ያላት ባለሙያ፣ ብዛት አንድ።

2.4 የኤሌክትሪክ ስራ ተቋራጭደረጃ 4

ሀ. አጠቃላይ የማመንጨት አቅም እስከ 1 ሜጋ ዋት ኃይል ያላቸው ማንኛቸውንም የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ ተቋማት የኤሌክትሪክ ግንባታ ሥራ አገልግሎት በሙሉ፣

ለ. አጠቃላይ የኤሌክትሪክ ሥራው የሚጠይቀው የኤሌክትሪክ ኃይል በአምፔር ወይም በኬቪኤ ከተዘረዘሩት የሥራ ወሰኖች ውስጥ አነስተኛነት በሚኖረው እስከ 630 ኬቪኤ የሚደርሱ ወይም ከቆጣሪ ቀጥሎ ያለው የኤሌክትሪክ ፍሰት መቆጣጠሪያ መገበሪያ አቅም እስከ 1000 አምፔርና እስከ 1 ኬቪ. የሚደርሱ ማንኛቸውንም የኤሌክትሪክ ግንባታ አገልግሎት ሥራዎች በሙሉ፣

ሐ. ከዚህ ደረጃ በታች ያሉ ሌሎች የኤሌክትሪክ ሥራዎችን በሙሉ ያካትታል።

2.4.1 ለኤሌክትሪክ ስራ ተቋራጭ ደረጃ 4 ከዚህ በታች በዝርዝር የተቀመጠው የሰው ኃይል መስፈርት መሟላት ይኖርበታል፣

ሀ. የኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽን ስራዎች የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ከኢ.ኢ.ባ ደረጃ "ለ" ያለው/ያላት ባለሙያ ብዛት አንድ፣



Federal Democratic Republic of Ethiopia Ethiopia Energy Authority

ለ. የኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽን ስራዎች የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ከኢ.ኢ.ባ ደረጃ "መ"ያለው/ያላት ባለሙያ ብዛት አንድ፣

❖ ከዚህ በላይ ከተቀመጠው የሙያ ብቃት ማረጋገጭ ያላቸው አንድ ባለሙያ ያቀረበ ድርጅትማለትም/ደረጃ "ሀ"/ ተጨማሪ አንድ ኤሌክትሪካል መሀንዲስ/ ኤሌክትሪሽያን /ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

## 2.5 የኤሌክትሪክ ስራ ተቋራጭደረጃ 5

ሀ. አጠቃላይ የማመንጨት አቅም እስከ 100 ኪ.ሎ ዋት የኃይል አቅም ያላቸው ማንኛቸውንም የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ ተቋማት የኤሌክትሪክ ግንባታ ሥራ አገልግሎት በሙሉ፣

ለ. አጠቃላይ የኤሌክትሪክ ሥራው የሚጠይቀው የኤሌክትሪክ ኃይል በአምፔር ወይም በኬቪኤ ከተዘረዘሩት የሥራ ወሰኖች ውስጥ አነስተኛነት በሚኖረው እስከ ከ630 ኬቪኤ የሆኑ ወይም ከቆጣሪ ቀጥሎ ያለው የኤሌክትሪክ ፍሰት መቆጣጠሪያ መገበሪያ አቅም እስከ 1000 አምፔርና እስከ 1 ኬቪ የሚደርሱ ማንኛቸውንም የኤሌክትሪክ ግንባታ አገልግሎት ሥራዎች በሙሉ፣

ሐ. ከዚህ ደረጃ በታች ያሉ ሌሎች የኤሌክትሪክ ሥራዎችን በሙሉ ያካትታል፡፡

2.5.1 ኤሌክትሪክ ስራ ተቋራጭ ደረጃ 5 ከዚህ በታችበዝርዝር የተቀመጠው የሰው ኃይል መሟላት ይኖርበታል፡፡

ሀ. የኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽን ስራዎች የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ከኢ.ኢ.ባ ደረጃ "ለ"ያለው/ያላት ባለሙያ ብዛት አንድ፣

ለ. የኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽን ስራዎች የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ከኢ.ኢ.ባ ደረጃ "ሠ" ያለው/ያላት ባለሙያ ብዛት አንድ፣

Federal Democratic Republic of Ethiopia Ethiopia Energy Authority

❖ ከዚህ በላይ ከተቀመጠው የሙያ ብቃት ማረጋገጭ ያላቸው አንድ ባለሙያ ያቀረበ ድርጅት ተጨማሪ አንድ ማለትም/ደረጃ ሀ/ ኤሌክትሪካል መሀንዲስ/ ኤሌክትሪሽያን /ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

## 2.6 የኤሌክትሪክ ስራ ተቋራጭደረጃ 6

ሀ. አጠቃላይ የማመንጨት አቅም እስከ 100 ኪሎ ዋት ኃይል ያላቸው ማንኛቸውንም የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ ተቋማት የኤሌክትሪክ ግንባታ ሥራ አገልግሎት በሙሉ፣

ለ. አጠቃላይ የኤሌክትሪክ ሥራው የሚጠይቀው የኤሌክትሪክ ኃይል በአምፔር ወይም በኬቪኤ ከተዘረዘሩት የሥራ ወሰኖች ውስጥ አነስተኛነት ያለውን እስከ 315 ኬቪኤ የሚደርሱ ወይም ከቆጣሪ ቀጥሎ ያለው የኤሌክትሪክ ፍሰት መቆጣጠሪያ መገበሪያ አቅም እስከ 500 አምፔርና እስከ 1 ኬቪ የሚደርሱ ማንኛቸውንም የኤሌክትሪክ ግንባታ አገልግሎት ሥራዎች በሙሉ፣

ሐ. ከዚህ ደረጃ በታች ያሉ ሌሎች የኤሌክትሪክ ሥራዎች በሙሉ ያካትታል፡፡

2.6.1 ለኤሌክትሪክ ስራ ተቋራጭ ደረጃ 6 ከዚህ በታችበዝርዝር የተቀመጠው የሰው ኃይል መስፈርት መሟላት ይኖርበታል

ሀ. የኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽን ስራዎች የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ከኢ.ኢ.ባ ደረጃ "ለ" ያለው/ያላት ባለሙያ፣ ብዛት አንድ

ለ. ኤሌክትሪሽያን ብዛት አንድ

## 2.7 የኤሌክትሪክ ስራ ተቋራጭደረጃ 7

ሀ. አጠቃላይ የማመንጨት አቅም እስከ 10 ኪሎዋት ኃይል ያላቸው ማንኛቸውንም የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ ተቋማት የኤሌክትሪክ ግንባታ ሥራ አገልግሎት በሙሉ፣



Federal Democratic Republic of Ethiopia Ethiopia Energy Authority

ለ. አጠቃላይ የኤሌክትሪክ ሥራው የሚጠይቀው የኤሌክትሪክ ኃይል በአምፔር ወይም በኬቪ.ኤ ከተዘረዘሩት የሥራ ወሰኖች ውስጥ አነስተኛነት ያለውን እስከ 100 ኬቪ.ኤ የሚደርሱ ወይም ከቆጣሪ ቀጥሎ ያለው የኤሌክትሪክ ፍሰት መቆጣጠሪያ መገበሪያ አቅም እስከ 160 አምፔርና እስከ 1 ኬቪ. የሚደርሱ ማንኛቸውንም የኤሌክትሪክ ግንባታ አገልግሎት ሥራዎች በሙሉ፣

ሐ. ከዚህ ደረጃ በታች ያሉ ሌሎች የኤሌክትሪክ ሥራዎች በሙሉ ያካትታል፡፡

2.7.1 ለኤሌክትሪክ ስራ ተቋራጭ ደረጃ 7 ከዚህ በታችበዝርዝር የተቀመጠው የሰው ኃይል መስፈርት መሟላት ይኖርበታል

ሀ. የኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽን ስራዎች የሙያ ብቃት ማረጋጫ የምስክር ወረቀትከኢ..ኢ.ባ ደረጃ "መ" ያለው/ያላት ባለሙያብዛት አንድ

ለ. ኤሌክትሪሽያን ብዛት አንድ፡፡

**2.8 የኤሌክትሪክ ስራ ተቋራጭደረጃ 8**

ሀ. አጠቃላይ የኤሌክትሪክ ሥራው የሚጠይቀው የኤሌክትሪክ ኃይል በአምፔር ወይም በኬቪ.ኤ ከተዘረዘሩት የሥራ ወሰኖች ውስጥ አነስተኛነት በሚኖረው እስከ 12 ኬቪ.ኤ የሚደርሱ ወይም ከቆጣሪ ቀጥሎ ያለው የኤሌክትሪክ ፍሰት መቆጣጠሪያ መገበሪያ አቅም ነጠላ ፌዝ እስከ 50 አምፔር ወይም ባለ ሦስት ፌዝ 20 አምፔርና እስከ 1 ኬቪ. የሚደርሱ ማንኛቸውንም የኤሌክትሪክ ግንባታ አገልግሎት ሥራዎችን በሙሉ፣

ለ. አጠቃላይ የማመንጨት አቅም እስከ 5 ኪ.ሎ ዋት አቅም ያላቸውን ማንኛቸውንም የመጠባበቂያ የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ ተቋማት የኤሌክትሪክ ግንባታ ሥራ አገልግሎትን በሙሉ ያካትታል፡፡

**2.8.1 ለኤሌክትሪክ ስራ ተቋራጭ ደረጃ 8 ከዚህ በታችበዝርዝር የተቀመጠው የሰው ኃይል መሟላት ይኖርበታል**

ሀ. የኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽን ስራዎች የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ከኢ..ኢ.ባ ደረጃ "ሠ" ያለው/ያላት ባለሙያ ብዛት አንድ፡፡

ለኤሌክትሪክ ሥራ ተቋራጭ የሚያስፈልጉ የቦታ አይነት ስፋት እና እቃዎች ዝርዝር

| ተ.ቁ. | የዕቃው አይነት ዝርዝር | የኤሌክትሪክ ሥራ ተቋራጭ ደረጃዎች | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ደረጃ 8 | ደረጃ 7 | ደረጃ 6 | ደረጃ 5 | ደረጃ 4 | ደረጃ 3 | ደረጃ 2 | ደረጃ 1 |
| | | መሟላት ያለበት ብ ዛ ት/ መ ጠ ን | | | | | | | |
| 1 | **የቢሮና የሥራ ማከናወኛ ቦታ ስፋት፣** | | | | | | | | |
| 1.1 | ቢሮ (በሜ.ካሬ) | ቋሚ አድራሻ | ቋሚ አድራሻ | ቋሚ አድራሻ | 12 | 20 | 30 | 50 | 60 |
| 1.2 | የሥራ ማከናወኛ ቦታ/ Workshop (በሜ.ካሬ) | | | | | 30 | 60 | 120 | 150 |
| **2** | **መኪና** | | | | | | | | |
| 2.1 | ፒክ አፕ መኪና | | | | | | 1 | 1 | 2 |
| 2. 2 | የእቃ ማውረጃና ማንሻ /ክሬን | | | | | | | | 1 |
| 3 | **የመገልገያ እቃዎችና የእጅ መሣሪያዎች** | | | | | | | | |
| 3.1 | Electrical tool box | - | 1 | 1 | 2 | 2 | 3 | 4 | 6 |
| 3.2 | Mechanical tool box | - | - | 1 | 2 | 2 | 2 | 4 | 6 |
| 3.3 | Hand Grinder | - | - | - | 1 | 1 | 2 | 3 | 4 |
| 3.4 | Welding machine | - | - | - | | 1 | 1 | 2 | 2 |
| 3.5 | Hand Drill | - | - | - | 1 | 1 | 2 | 3 | 4 |
| 3.6 | Crimping tools up to 300 sq.mm | - | - | - | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 |
| 3.7 | Crimping tools above 300 sq.mm | - | - | - | - | 1 | 1 | 1 | 1 |
| 3.8 | Pipe threader | - | - | - | - | - | - | 1 | 1 |
| 3.9 | Pipe vice | - | - | - | - | - | - | 1 | 1 |
| 3.10 | Pipe wrenches 12" -36" | - | - | - | - | - | - | 1 | 1 |
| 3.11 | Pipe cutter | - | - | - | 1 | 1 | 1 | 2 | 2 |
| 3.12 | Cable cutter | - | 1 | 1 | 1 | 1 | 2 | 2 | 3 |

| ተ.ቁ. | የዕቃው አይነት ዝርዝር | የኤሌክትሪክ ሥራ ተቋራጭ ደረጃዎች | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ደረጃ 8 | ደረጃ 7 | ደረጃ 6 | ደረጃ 5 | ደረጃ 4 | ደረጃ 3 | ደረጃ 2 | ደረጃ 1 |
| | | መሟላት ያለበት ብ ዛ ት/ መ ጠ ን | | | | | | | |
| 3.13 | Hot air gun/ Blow torch | - | - | - | - | - | 1 | 1 | 1 |
| 3.14 | Steel or Almunium ladder of (4m, 6m, 8m, 11m) | - | 1 | 1 | 2 | 2 | 3 | 3 | 4 |
| 3.15 | Scaffolding | - | - | - | - | - | - | 1 | 1 |
| 3.16 | Winch 5 ton | - | - | - | - | - | - | 1 | 1 |
| 3.17 | Bench vice | - | - | 1 | 1 | 1 | 2 | 2 | 2 |
| 3.18 | Drum jack / Underground cable rollers/ | - | - | - | - | - | - | 1 | 1 |
| 3.19 | Lifting jack or Hoist cran of 5 ton | - | - | - | - | - | 1 | 1 | 1 |
| 3.20 | Torque wrench up to 100 Nn | - | - | - | - | - | 1 | 1 | 1 |
| 3.21 | Hole saw | - | - | - | - | - | 1 | 1 | 1 |
| 3.22 | Grounding device for stringing operation | - | - | - | - | - | 1 | 1 | 1 |
| 3.23 | Pipe (Tube bender) | - | - | - | - | 1 | 1 | 1 | 1 |
| 3.24 | Bench Electrical cutting machine | - | - | - | - | - | - | 1 | 1 |
| 3.25 | Hydraulic press machine with set of dies above 95 sq.mm | - | - | - | - | - | 1 | 1 | 1 |
| 3.26 | Jimpole (4-10)mts* | - | - | - | - | 1 | 1 | 1 | 1 |
| 3.27 | Hydraulic press machine with set of dies motor operated | - | - | - | - | - | 1 | 1 | 1 |
| 3.28 | Pulleys* | - | - | - | - | - | 1 | 1 | 1 |
| 3.29 | wooden, concrete or steel climbing shoes in paires | - | - | - | - | 2 | 4 | 6 | 8 |

| ተ.ቁ. | የዕቃው አይነት ዝርዝር | የኤሌክትሪክ ሥራ ተቋራጭ ደረጃዎች | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ደረጃ 8 | ደረጃ 7 | ደረጃ 6 | ደረጃ 5 | ደረጃ 4 | ደረጃ 3 | ደረጃ 2 | ደረጃ 1 |
| | | መሟላት ያለበት ብ ዛ ት/ መ ጠ ን | | | | | | | |
| 4 | **ማለ ኪያ መሣሪ ያ ዎች** | | | | | | | | |
| 4.1 | Multimeter | 1 | 1 | 1 | 2 | 2 | 3 | 4 | 6 |
| 4.2 | Insulation tester up to 1 kV | - | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 2 |
| 4.3 | Insulation tester up to 5 kV | - | - | - | - | 1 | 1 | 1 | 1 |
| 4.4 | Clamp on Ammeter | - | - | - | - | 1 | 1 | 1 | 1 |
| 4.5 | Megger up to 5kV | - | - | - | - | - | | 1 | 1 |
| 4.6 | phase sequence tester | - | - | - | - | 1 | 1 | 1 | 1 |
| 4.7 | earth resistance tester | - | - | - | - | 1 | 1 | 1 | 1 |
| 4.8 | HV detector | - | - | - | - | - | 1 | 1 | 1 |
| 5 | **የደህንነት መከላከያ መሣሪያዎች** | | | | | | | | |
| 5.1 | የደህንነት መከላከያ ቀበቶ | - | - | - | 1 | 2 | 2 | 3 | 4 |
| 5.2 | የደህንነት መከላከያ የራስ ቆብ | - | - | - | 1 | 2 | 2 | 3 | 4 |
| 5.3 | የእጅ የቆዳ ጓንቲ | - | - | - | 1 | 1 | 2 | 3 | 4 |
| 5.4 | የእጅ የፕላስቲክ ጓንቲ | - | - | - | 1 | 1 | 2 | 3 | 4 |
| 5.5 | Leather apron | - | - | - | - | - | 2 | 3 | 4 |
| 5.6 | Eye Goggles | - | - | 1 | 1 | 1 | 2 | 2 | 2 |
| 5.7 | Micrometer (0-100 mm) /Collper | - | - | - | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 |

የሚከተሉት መሣሪያዎች ለየእርከናቹ አስፈላጊ ባይሆኑም በሥራ ቦታ ላይ ተቋራጩን ሲያስፈልጉት በሚችሉበት ወቅት በኪራይ ወይም በሌላ ዘዴ ሊያሟላቸው ይችላል ተብሎ ይታሰባል፡፡

Pilot Wire 100 m
Lifting jack or Hoist cran of 10 ton
Hydraulic press machine with set of dies above 95 sq. mm
Oxygen Acetelyen welding set

| ተ.ቁ. | የዕቃው አይነት ዝርዝር | የኤሌክትሪክ ሥራ ተቋራጭ ደረጃዎች | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ደረጃ 8 | ደረጃ 7 | ደረጃ 6 | ደረጃ 5 | ደረጃ 4 | ደረጃ 3 | ደረጃ 2 | ደረጃ 1 |
| | | መሟላት ያለበት ብ ዛ ት/ መ ጠ ን | | | | | | | |
| Pilot wire 100 mt<br>Head sacks for conductor (11 to breaking load)<br>Portable disel generater of various capacitys | | | | | | | | | |

ማሳሰቢያ:-

- የስራ ቦታ በኪራይ፤በሊዝ ወይም የባለቤትነት ማረጋገጫ ካርታ መቅረብ ይኖርበታል::
- ተሽከርካሪ ሊብሬ በድርጅቱ ወይም ሶል ካምፓኒ ከሆነ በባለቤቱ ስም መሆን አለበት::
- ክሬን በኪራይ ውል ይቻላል::
- ካርታ ወይም ሊብሬ በባለፍቃዱ የትዳር አጋር ከሆነ የጋብቻ ውል መቅረብ ይኖርበታል::

## 3.ሌክትሮ ሜካኒካል ሥራ ተቋረጭ (50330)

የኤሌክትሮ መካኒካል ሥራ ተቋራጭ 8 ደረጃዎች አሉት፡፡

ማንኛዉም ድርጅት ለሚፈልገዉ ደረጃ የተቀመጠዉን መስፈርት ሲያሟላ ብቻ ይስተናገዳል፣

- ነባር ድርጅት በእድሳት ወቅት ቀደም ሲል በወሰደው ደረጃ ያከናወናቸዉን ስራዎች የሚገልፅ የሥራ አፈጻጸም/ውል ገባቸዉን የኮንትራት ሥራዎች በስምምነቱ መሠረት ጨርሶ ማስረከቡን ወይም በውሉ መሰረት እየሰራ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ሲያቀርብ /በኢንስፔክሽን ሲረጋገጥ እና ሌሎች መስፈርቶች መሟላታቸው ተረጋግጦ ብቃቱን ማሳደስ፣ ደረጃ መቀነስ ወይም ብቃቱ ሊሰረዝ ይችላል፡፡
- ከደረጃ 1-4 የብቃት ማረጋገጫ ለሚፈልጉ ድርጅቶች እንደ አስፈላጊነቱ የቅድመ ኢንስፔክሽን ከተሰራ በኋላ መስፈርቱ መሟላቱ ሲረጋገጥ ይስተናገዳሉ፡፡
- አንድ ድርጅት ካለበት ደረጃ ወደ ቀጣይ ደረጃ ማሳደግ ቢፈልግ ለቀጣይ ደረጃ የሚያስፈልጉ መስፈርቶችን ከማሟላት በተጨማሪ በነበረው ደረጃ የሰራቸውን ፕሮጀክቶች የተሟላ (የፕሮጀክት ኮንትራት ውል፣ የክፍያ ሰነድ እና የአፈጻጸም ማስረጃ) በሚከተለው ዝርዝር መሰረት ማቅረብ ይጠበቅበታል፤
    - ➢ ከደረጃ 8፣7 እና 6 ወደ ደረጃ 5 ለማደግ ድርጅቱ በሚያቀርበው የሰው ኃይል እና ለየደረጃው የተቀመጡ መሳሪያዎችን በማሟላት እድገት ማግኘት ይቻላል
    - ➢ ከደረጃ 5 ወደ ደረጃ 4 ድርጅቱ የሰራቸው ፕሮጀክቶች ጠቅላላ ካፒታል አንድ ሚሊየን ብር እና ከዚያ በላይ
    - ➢ ከደረጃ 4 ወደ ደረጃ 3 ድርጅቱ የሰራቸው ፕሮጀክቶች ጠቅላላ ካፒታል አምስት ሚሊየእና ከዚያ በላይ
    - ➢ ከደረጃ 3 ወደ ደረጃ 2 ድርጅቱ የሰራቸው ፕሮጀክቶች ጠቅላላ ካፒታል አሥር ሚሊየን ብር እና ከዚያ በላይ



Federal Democratic Republic of Ethiopia Energy Authority

- ከደረጃ 2 ወደ ደረጃ 1 (አንድ) ድርጅቱ የሰራቸው ፕሮጀክቶች ጠቅላላ ካፒታል ሃያ አምስት ሚሊየን ብር እና ከዚያ በላይ መሆን ይኖርበታል

ማንኛውም ድርጅት ከደረጃ አምስት፣ ከደረጃ አራት ወይም ደረጃ ሶስት ወደ ደረጃ 2 ወይም ወደ ደረጃ አንድ ለማግኘት ለደረጃው የተቀመጡትን መስፈርቶች እና

- የገባባቸውን የኮንትራት ስራዎች በስምምነቱ መሠረት ጨርሶ
    - የፕሮጀክት አፈጻጸም ከሟላ የደረጃ ዕድገቱን ማግኘት ይችላል፡፡
    - *በኮንስትራክሽን ከኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን /EIC/ የንግድ ምዝገባ ያላቸው ድርጅቶች ወይም ግለሰቦች ኤሌክትሮሜካኒካል ከደረጃ አንድ ውጭ ብቃት ማረጋገጫ መውሰድ እንደማይችሉ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት አዋጅ 769/2004 ይደነግጋል፡፡ስለዚህ ደረጃ አንድ ብቻ መውሰድ ይችላሉ፡፡*

እያንዳንዱ ደረጃ ከዚህ የሚከተለው የሰው ሀይል መስፈርት ይኖረዋል፡-

**3.1 ኤሌክትሮ ሜካኒካል ሥራ ተቋረጭ ደረጃ 1**

ሀ. አንድ ኤሌክትሪካል መሀንዲስ 8 ዓመት ቀጥተኛ የስራ ልምድ ያለው/ያላት

ለ. አንድ ሜካኒካል/ኤሌክትሮመካኒካል መሀንዲስ 8 ዓመት ቀጥተኛ የስራ ልምድ ያለው/ያላት

ሐ. አንድ ኤሌክትሪካል መሀንዲስ 4 ዓመት ቀጥተኛ የስራ ልምድ ያለው/ያላት

መ. አንድ ሜካኒካል/ኤሌክትሮመካኒካል መሀንዲስ 2 ዓመት ቀጥተኛ የስራ ልምድ ያለው/ያላት

ሠ. አንድ ኤሌክትሪሻን ወይም ሜካኒክ 10 ዓመት እና ከዚያ በላይ ቀጥተኛ የስራ ልምድ ያለው/ያላት፣

ረ. አንድ ኤሌክትሪሻን ወይም ሜካኒክ 5 ዓመት እና ከዚያ በላይ ቀጥተኛ የስራ ልምድ ያለው/ያላት፣

ሰ. አንድ ኤሌክትሪሻን ወይም ሜካኒክ 3 ዓመት እና ከዚያ በላይ ቀጥተኛ የስራ ልምድ ያለው/ያላት፣

ሸ. ሁለት ጀማሪ ኤሌክትሪሻን ወይም ሜካኒክ፣

*ለደረጃ 1 በኤሌክትሪክ የሙያ መስክ ከተጠቀሱት ባለሙያዎች ውስጥ ቢያንስ አንድ አንድ ባለሙያ በደረጃ “ሀ” እና “መ”ከኢ.ኢ.ባ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት የወሰደ/ የወሰደች መሆን አለባቸው።*

### 3.2 ኤሌክትሮ ሜካኒካል ሥራ ተቋረጭ ደረጃ 2

ሀ. አንድ ኤሌክትሪካል መሀንዲስ 7 ዓመት ቀጥተኛ የስራ ልምድ ያለው፣

ለ. አንድ ሜካኒካል/ኤሌክትሮመካኒካል መሀንዲስ 7 ዓመት ቀጥተኛ የስራ ልምድ ያለው፣

ሐ. አንድ ኤሌክትሪሻን 8 ዓመት እና ከዚያ በላይ ቀጥተኛ የስራ ልምድ ያለው፣

መ. አንድ ኤሌክትሪሻን ወይም ሜካኒክ 3 ዓመት እና ከዚያ በላይ ቀጥተኛ የስራ ልምድ ያለው፣

ሠ. ሁለት ጀማሪ ኤሌክትሪሻን ወይም ሜካኒክ፣

ሰ. ለደረጃ 2 በኤሌክትሪክ የሙያ መስክ ከተጠቀሱት ባለሙያዎች ውስጥ ቢያንስ አንድ አንድ ባለሙያ በደረጃ "ሀ" እና "ሠ"ከኢ.ኢ.ባ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት የወሰደ/ የወሰደች መሆን አለባቸው።

### 3.3 ኤሌክትሮ ሜካኒካል ሥራ ተቋረጭ ደረጃ 3

ሀ. አንድ ኤሌክትሪካል መሀንዲስ 6 ዓመት ቀጥተኛ የስራ ልምድ ያለው፣

ለ. አንድ ሜካኒካል/ኤሌክትሮመካኒካል መሀንዲስ ከ 5 ዓመት በላይ ቀጥተኛ የስራ ልምድ ያለው፣

ሐ አንድ ሜካኒክ/ኤሌክትሪሻን 4 ዓመት እና ከዚያ በላይ ቀጥተኛ የስራ ልምድ ያለው፣

መ. ሁለት ጀማሪ ኤሌክትሪሻን ወይም ሜካኒክ፣

ሠ. ለደረጃ 3 በኤሌክትሪክ የሙያ መስክ ከተጠቀሱት ባለሞያዎች ውስጥ ቢያንስ አንድ አንድ ባለሞያ በደረጃ "ሀ" ከኢ.ኢ.ባ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት የወሰደ/ የወሰደች መሆን አለባቸው።

### 3.4 ኤሌክትሮ ሜካኒካል ሥራ ተቋረጭ ደረጃ 4

ሀ. አንድ ኤሌክትሪካል መሀንዲስ 5 ዓመት ቀጥተኛ የስራ ልምድ ያለው፣

ለ. አንድ ሜካኒካል/ኤሌክትሮመካኒካል መሀንዲስ ከ 4 ዓመት በላይ ቀጥተኛ የስራ ልምድ ያለው፣

ሐ. አንድ ኤሌክትሪሻን 4 ዓመት እና ከዚያ በላይ ቀጥተኛ የስራ ልምድ ያለው፣

መ. አንድ ጀማሪ ኤሌክትሪሻን ወይም ሜካኒክ፣

Federal Democratic Republic of Ethiopia Ethiopia Energy Authority

ሠ. ለደረጃ 5 በኤሌክትሪክ የሙያ መስክ ከተጠቀሱት ባለሞያዎች ውስጥ ቢያንስ አንድ አንድ ባለሞያ በደረጃ “ለ” እና “መ ” ከኢ.ኢ.ባ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት የወሰደ/ የወሰደች መሆን አለባቸው፡፡

### 3.5 ኤሌክትሮ ሜካኒካል ሥራ ተቋረጭ ደረጃ 5

**ሀ.** አንድ ኤሌክትሪካል መሀንዲስ 4 ዓመት ቀጥተኛ የስራ ልምድ ያለው፣

**ለ.** አንድ መካኒካል / ኤሌክትሮመካኒካል መሀንዲስ 3ዓመት የስራ ልምድ ያለዉ/ ሜካኒክ 4 ዓመት እና ከዚያ በላይ ቀጥተኛ የስራ ልምድ ያለው፣

**ሐ.** አንድ ኤሌክትሪሻን/ 4 ዓመት እና ከዚያ በላይ ቀጥተኛ የስራ ልምድ ያለው፣

**መ.** አንድ ጀማሪ ሜካኒክ፣

**ሠ.** ለደረጃ 5 በኤሌክትሪክ የሙያ መስክ ከተጠቀሱት ባለሞያዎች ውስጥ ቢያንስ አንድ አንድ ባለሞያ በደረጃ “ለ” እና “ሠ ” ከኢ.ኢ.ባ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት የወሰደ/ የወሰደች መሆን አለባቸው፡፡

### 3.6 ኤሌክትሮ ሜካኒካል ሥራ ተቋረጭ ደረጃ 6

ሀ. አንድ ኤሌክትሪሻን 4 ዓመት እና ከዚያ በላይ ቀጥተኛ የስራ ልምድ ያለው፣

ለ. አንድ መካኒካል / ኤሌክትሮመካኒካል ቴክኒሽን ወይም

ሐ. አንድ ሜካኒክ/ኤሌክትሪሻን 2 ዓመት እና ከዚያ በላይ ቀጥተኛ የስራ ልምድ ያለው፣

መ. ለደረጃ 6 በኤሌክትሪክ የሙያ መስክ ከተጠቀሱት ባለሞያዎች ውስጥ ቢያንስ አንድ አንድ ባለሞያ በደረጃ “ለ” ከኢ.ኢ.ባ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት የወሰደ/ የወሰደች መሆን አለባቸው፡፡

### 3.7 ኤሌክትሮ ሜካኒካል ሥራ ተቋረጭ ደረጃ 7

ሀ. አንድ ኤሌክትሪሻን 3 ዓመት እና ከዚያ በላይ ቀጥተኛ የስራ ልምድ ያለው፣

ለ. አንድ ሜካኒክ/ ኤሌክትሮመካኒካል ቴክኒሽን 0 ዓመት እና ከዚያ በላይ ቀጥተኛ የስራ ልምድ ያለው፣

ሐ. ለደረጃ 7 በኤሌክትሪክ የሙያ መስክ ከተጠቀሱት ባለሞያዎች ውስጥ ቢያንስ አንድ አንድ ባለሞያ በደረጃ "መ" ከኢ.ኢ.ባ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት የወሰደ/ የወሰደች መሆን አለባቸው።

### 3.8 ኤሌክትሮ ሜካኒካል ሥራ ተቋረጭ ደረጃ 8

**ሀ**. አንድ ኤሌክትሪሻን 1 ዓመት እና ከዚያ በላይ ቀጥተኛ የስራ ልምድ ያለው፣

**ለ**. አንድ ሜካኒክ/ኤሌክትሮመካኒካል ቴክኒሽን 0 ዓመት እና ከዚያ በላይ ቀጥተኛ የስራ ልምድ ያለው፣

**ሐ**. ለደረጃ 8 በኤሌክትሪክ የሙያ መስክ ከተጠቀሱት ባለሞያዎች ውስጥ ቢያንስ አንድ ባለሞያ በደረጃ "ሠ" ከኢ.ኢ.ባ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊ የወሰደ/ የወሰደች መሆን አለባቸው።

ለኤሌክተሮ ሜካኒካል ስራ ተቋራጭነት ብቃት ማረጋገጫ የሚያስፈልጉ ዝቅተኛ የመገልገያ መሳሪያዎች መስፈርት/

(Mimimum Equipment Requirement for competency certificate of electro mechanical contractors)

| | Description | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ቢሮ (በሜ.ካሬ) | 60 | 50 | 30 | 20 | 12 | | | |
| 2 | የሥራ ማከናወኛ ቦታ/ Workshop ((በሜ.ካሬ)) | 150 | 130 | 60 | 30 | | | | |
| 3 | Crane / Telscopic crane------------ 20 ton (**Optional**) | | -- | -- | -- | -- | | | |
| 4 | Telscopic crane /Carne ----------- 6ton | 1 | | | -- | -- | | | |
| 5 | Truck mounted crane----6 ton | 1 | 1 | | | | | | |
| 6 | Forclift (**Oprional**) | | | | | -- | | | |
| 7 | Heavy duty truck-----5-10 ton (**optional**) | | | | | -- | | | |
| 8 | Light duty truck -------3-5 ton | 1 | 1 | 1 | | -- | | | |
| 9 | Pick up | 1 | 1 | 1 | 1 | | | | |
| 10 | Electrical tool kit | 3 | 2 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | |
| 11 | Mechnaical tool kit | 2 | 2 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | |
| 12 | Welding machine | 3 | 2 | 2 | 1 | 1 | 1 | 1 | |
| 13 | Oil tester | 1 | 1 | 1 | 1 | | | | |
| 14 | Hydraulic compression tool | 3 | 2 | 1 | 1 | | | | |
| 15 | Rachet cable cutter | 2 | 2 | 1 | 1 | | | | |
| 16 | Sing loops------------- 5 ton | 5 | 3 | 2 | 1 | | | | |

Federal Democratic Republic of Ethiopia Ethiopia Energy Authority

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 17 | Sing loops------------- 3 ton | 5 | 3 | 2 | 1 | | | | |
| 18 | Mobil heavy duty workshop (optional) | | -- | -- | -- | | | | |
| 19 | Mobile Van workshop | 1 | 1 | 1 | -- | | | | |
| 20 | 3x380x200V.10kVA Generator (optional) | | | | | | | | |
| 21 | Service Pully 2.5 ton | 2 | 1 | 1 | -- | | | | |
| 22 | Service Pully 1.5 ton | 2 | 1 | 1 | 1 | | | | |
| 23 | Scaffolding 30 mts. | 1 | -- | -- | -- | | | | |
| 24 | Scaffolding 15 mts | 1 | 1 | 1 | -- | | | | |
| 25 | Extension Ladder | 3 | 2 | 1 | 1 | | | | |
| 26 | Chain hoist 5 to | 2 | 1 | -- | -- | | | | |
| 27 | Chain hoist 3 ton | 2 | 1 | 1 | 1 | | | | |
| 28 | Conductor pulling machine with Tensioner 10-20 ton | 1 | 1 | -- | -- | | | | |
| 29 | Conductor pulling machine with Tensioner 4-6 ton | 1 | 1 | 1 | 1 | | | | |
| 30 | Volt meter | 2 | 2 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 |
| 31 | Line tester/meager/ | 2 | 2 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 |
| 32 | Hand grinding machine | 3 | 2 | 1 | 1 | | | | |
| 33 | Manual steel cutting machine | 1 | 1 | | | | | | |
| 34 | Pully lift | 1 | 1 | 1 | | | | | |
| 35 | Tools set | 3 | 2 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 |
| 36 | Vice | 1 | 1 | | | | | | |

ማሳሰቢያ: -

- የስራ ቦታ በኪራይ፣በሊዝ ወይም የባለቤትነት ማረጋገጫ ካርታ መቅረብ ይኖርበታል፡፡
- ተሸከርካሪ ሊብሬ በድርጅቱ ወይም ሶል ካምፓኒ ከሆነ በባለቤቱ/በድርጅቱ ንግዱ/ ስም መሆን አለበት፡፡
- ክሬን በኪራይ ውል ይቻላል፡፡
- ካርታ ወይም ሊብሬ በባለፍቃዱ የትዳር አጋር ከሆነ የጋብቻ ውል መቅረብ ይኖርበታል፡፡

## ክፍል ሦስት

## የማማከር አገልግሎት

### 4. ኤሌክትሪካል ኢንጂነሪንግ የማማከር አገልግሎት (88721)

**ኤሌክትሪካል ኢንጂነሪንግ ማማከር አገልግሎት አምስት ደረጃዎች አሉት**

| ደረጃዎች | የሚያስፈልግው የሰው ኃይል | የገንዘብ መጠን በብር | የቢሮ ስፋት በካሬ ሜትር | እቃዎች እና መሳሪያዎች | እቃዎች እና መሳሪያዎች ብዛት |
|---|---|---|---|---|---|
| ደረጃ-I | 1. ኤሌክትሪካል መሀንዲስ 12 ዓመት የስራ ልምድ ያለው ፡- 6 ዓመት ወይም ከዚያ በላይ በማማከር/6 ዓመት ወይም ከዚያ በላይ በፋብሪካ በክትትል እና ቁጥጥር, ተካላ, ጥገና እና ፍተሻ ,የሰራ/የሰራች ብዛት አንድ | 200,000 | 50 | ኮምፒዩተር | 5 |
| | 2. በኤሌክትሪካል ምህንድስና ቢያንስ የ10 ፕሮጀክቶች ዲዛይን የሰራ ወይም ተመሳሳይ የስራ ልምድ ያለው/ያላት ብዛት አንድ | | | ወንበር፤ጠረንጴዛ | 5 |
| | 3. ጀማሪ ኤሌክትሪካል መሀንዲስ ብዛት አንድ | | | ፕሪንተር፣ ፎቶኮፒ እና ስካነር ፕሎተር | እያንዳንዱ ብዛት አንድ |
| | | | | መኪና | 2 |
| | 4. ፀሀፊ<br>*ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት ሦስት መሀንዲሶች ቢያንስ ሁለቱ ከኢ.ኢ.ባ የኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽ ደረጃ ሀ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ያላቸው መሆን ይኖርባቸዋል። | | | ላፕቶፕ | 1 |

Federal Democratic Republic of Ethiopia Ethiopia Energy Authority

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ደረጃ-II | 1 . ኤሌክትሪካል መሀንዲስ 8 ዓመት የስራ ልምድ ያለው :- 4 ዓመት ወይም ከዚያ በላይ በማማከር/4 ዓመት ወይም ከዚያ በላይ በፋብሪካ በክትትል እና ቁጥጥር, ተካላ, ጥገና እና ፍተሻ ,የሰራ/የሰራች ብዛት አንድ | 150,000 | 30 | ከፐምፒዩተር | 4 |
| | 2. በኤሌክትሪካል ምህንድስና ቢያንስ የ8 ፕሮጀክቶች ዲዛይን የሰራ ወይም ተመሳሳይ የስራ ልምድ ያለው/ያላት ብዛት አንድ | | | ፕሪንተር፣ ፎቶኮፒ እና ስካነር | እያንዳንዱ ብዛት አንድ |
| | 3. ጀማሪ ኤሌክትሪካል መሀንዲስ ብዛት አንድ | | | ወንበር፣ጠረንጴዛ | 4 |
| | 4. ፀሀፊ<br>ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት ሦስት መሀንዲሶች ቢያንስ ሁለቱ ከኢ.ኢ.ባ የኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽ አንድ ደረጃ ሀ እና አንድ ደረጃ ለ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ያላቸው መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ | | | | |
| ደረጃ- III | 1. ኤሌክትሪካል መሀንዲስ 6 ዓመት የስራ ልምድ ያለው :- 3 ዓመት ወይም ከዚያ በላይ በማማከር/3 ዓመት ወይም ከዚያ በላይ በፋብሪካ በክትትል እና ቁጥጥር, ተካላ, ጥገና እና ፍተሻ ,የሰራ/የሰራች ብዛት አንድ | 100,000 | 25 | ኮምፒዩተር | 3 |
| | 2. በኤሌክትሪካል ምህንድስና ቢያንስ የ6 ፕሮጀክቶች ዲዛይን የሰራ ወይም ተመሳሳይ የስራ ልምድ ያለው/ያላት ብዛት አንድ | | | ፕሪንተር፣ ፎቶኮፒ እና ስካነር ፕሎተር | እያንዳንዱ ብዛት አንድ |
| | 3.ጀማሪ ኤሌክትሪካል መሀንዲስ ብዛት አንድ | | | | |
| | 4. ፀሀፊ<br>ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት ሦስት መሀንዲሶች ቢያንስ ሁለቱ ከኢ.ኢ.ባ የኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽ አንድ ደረጃ ሀ እና አንድ ደረጃ መ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ያላቸው መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ | | | | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | |
| ደረጃ-IV | 1 . ኤሌክትሪካል መሀንዲስ 4 ዓመት የስራ ልምድ ያለው :- 2 ዓመት ወይም ከዚያ በላይ በማማከር/ 2 ዓመት ወይም ከዚያ በላይ በፋብሪካ በክትትል እና ቁጥጥር, ተካላ, ጥገና እና ፍተሻ ,የሰራ/የሰራች ብዛት አንድ | 75,000 | 20 | ኮምፒዩተር | 2 |
| | 2. . በኤሌክትሪካል ምህንድስና ቢያንስ የ5 ፕሮጀክቶች ዲዛይን የሰራ ወይም ተመሳሳይ የስራ ልምድ ያለው/ያላት ብዛት አንድ | | | ፕሪንተር፣ ፎቶኮፒ እና ስካነር | እያንዳንዱ ብዛት አንድ |
| | 3 . ጀማሪ ኤሌክትሪካል መሀንዲስ ብዛት አንድ | | | ወነወበር እና ጠረንጴዛ | 4 |
| | 4. ፀሀፊ<br>ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት ሦስት መሀንዲሶች ቢያንስ አንድ ከኢ.ኢ.ባ የኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽ አንድ ደረጃ ሀ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ያለው/ያላት መሆን አለበት:: | | | | |
| ደረጃ- V | 1. ኤሌክትሪካል መሀንዲስ 3 ዓመት የስራ ልምድ ያለው :- 1 ዓመት ወይም ከዚያ በላይ በማማከር/ 2 ዓመት ወይም ከዚያ በላይ በፋብሪካ በክትትል እና ቁጥጥር, ተካላ, ጥገና እና ፍተሻ ,የሰራ/የሰራች ብዛት አንድ | 50,000 | 12 | ኮምፒዩተር | 2 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | |
| | 2 ጀማሪ ኤሌክትሪካል መሀንዲስ ብዛት አንድ | | | ወነበር እና ጠረንፔዛ | 3 |
| | 4. ፀሀፊ<br>ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት ሦስት መሀንዲሶች ቢያንስ አንድ ከኢ.ኢ.ባ የኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽ አንድ ደረጃ ለ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ያለው/ያላት መሆን አለበት፡፡ | | | ፕሪንተርና ፎቶኮፒ/ስካነር | 1 |

Federal Democratic Republic of Ethiopia Ethiopia E... Authority

5. ከኢንጂነሪንግ ውጭ በኢነርጂ የማማከር አገልግሎት/88770/ መሟላት የሚገባው መስፈርት

| የንግድ ኮድ (88770) | የሰው ኃይል መስፈርት | የስራ ቦታ በካሜ | መገልገያ እቃዎች እና መሳሪያዎች |
|---|---|---|---|
| | 1 በህግ በዶክትሬት ዲግሪ የተመረቀ/የተመረቀች እና አንድ አመት በኢነርጂ የማማከር አገልግሎት/ማኔጅመንት/በኢነርጂዙሪያ የሰራ/የሰራች ወይም በህግ የሁለተኛ ዲግሪ የተመረቀ/የተመረቀች እና ሦስት አመት በኢነርጂ የማማከር አገልግሎት/ማኔጅመንት/በኢነርጂዙሪያ የሰራ/የሰራች ወይም በህግ የመጀመሪያ ዲግሪ የተመረቀ/የተመረቀች እና አምስት ዓመት በኢነርጂ የማማከር አገልግሎት/ማኔጅመንት/በኢነርጂዙሪያ የሰራ/የሰራች<br>2. በኢኮኖሚክስ/ኢነርጂ ኢኮኖሚክስ/ በዶክትሬት ዲግሪ የተመረቀ/የተመረቀች እና ሁለት አመት በኢነርጂ የማማከር አገልግሎት/ማኔጅመንት/በኢነርጂዙሪያ የሰራ/የሰራች ወይም በኢኮኖሚክስ/ኢነርጂ ኢኮኖሚክስ/ የሁለተኛ ዲግሪ የተመረቀ/የተመረቀች እና አራት አመት በኢነርጂ የማማከር አገልግሎት/ማኔጅመንት/በኢነርጂዙሪያ የሰራ/የሰራች ወይም በኢኮኖሚክስ/ኢነርጂ ኢኮኖሚክስ/ የመጀመሪያ ዲግሪ የተመረቀ/የተመረቀች እና ስድስት ዓመት በኢነርጂ የማማከር አገልግሎት/ማኔጅመንት/በኢነርጂዙሪያ የሰራ/የሰራች<br>3.በማናጅመንት በዶክትሬት ዲግሪ የተመረቀ/የተመረቀች እና ሁለት አመት በኢነርጂ | 12 | ኮምፒዩተር |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | የማማከር አገልግሎት/ማኔጅመንት/በኢነርጂዙሪያ የሰራ/የሰራች ወይም በማናጅመንት የሁለተኛ ዲግሪ የተመረቀ/የተመረቀች እና አራት አመት በኢነርጂ የማማከር አገልግሎት/ማኔጅመንት/በኢነርጂዙሪያ የሰራ/የሰራች ወይም በማናጅመንት የመጀመሪያ ዲግሪ የተመረቀ/የተመረቀች እና ስድስት ዓመት በኢነርጂ የማማከር አገልግሎት/ማኔጅመንት/በኢነርጂዙሪያ የሰራ/የሰራች<br>4.ፀሀፊ | | |

## ክፍል አራት
## የተለያዩ ማብራሪያዎች

### 6. ልዩ ድንጋጌዎች

- የሥራ ልብስና የተሟላ የደህንነት ትጥቅ ከፆታቸው አንጻር የጐንዮሽ ጉዳት እንዳያመጣ የወንዱንም የሴቱንም ፍላጐት ያካተተ መሆኑን መረጋገጥ አለበት፡፡
- በቂና ብቃት ያለው የሰው ኃይል ሲደራጅ ተዋጽኦው በተቻለ መጠን ሁለቱንም ፆታ ያካተተ ቢሆን የመረጣል፡፡
- የሥራ ሪከርዶችና ሰነዶች በፆታ ተለይተው የተዘጋጁ መሆን አለባቸው፡፡

### 7. ጥፋት ስለመፈፀም

ከዚህ መመሪያ አፈፃፀም ጋር በተያያዘ የሚፈፀም ማንኛውም ጥፋት በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 980/2010 ድንጋጌዎች መሰረት አስፈላጊው አስተዳደራዊና የወንጀል ቅጣት ሊወሰድበት ይችላል፡፡

### 8. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 980/2010 በሚሸፍናቸው ለኤሌክትሪክ እና ኤሌክትሪክ ነክ የንግድ ሥራ መስኮች በሚወጡ የንግድ ብቃት ማረጋገጫዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

### 9. መመሪያውን ስለማሻሻል

አወጪው መሥሪያ ቤት ይህን መመሪያ አስፈላጊ ሆኖ ባገኘዉ ጊዜ ሊያሻሽለዉ ይችላል፡፡

### 10. የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከሐምሌ 1 ቀን 2010 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**

**የኢትዮጵያ ኢነርጂ ባለስልጣን**

ጌታሁን ሞገስ

ዋና ዳይሬክተር